# የኦዲት ግኝት መረጃ አመላካች

**መረጃ ሰጪው፡ -** የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

**ኦዲት ተደራጊ፡ -** የግብርና ትራንስፎርሜሽን ኤጀንሲ

**ኦዲት የተደረገው የበጀት ዓመት፡ -** የ2013 በጀት ዓመት

**የኦዲት አካባቢ፡ -** የፋይናንስና ህጋዊነት ኦዲት

**የኦዲት ግኝት፡ -**

## 1. ለታለመ ዓላማ ስራ ላይ ያልዋለና ከተገቢው የገንዘብ ምንጭ ያልተከፈለ ብር 30,375.86 ወጪ፣

### 1.1 ሁኔታ

ለግብርና ትራንስፎርሜሺን ኤጀንሲ ኦሮሚያ ቅርንጫፍ ቢሮ የሚውል የቢሮ ፓርቲሺን ስራ ለማስራት በድምሩ የ**ብር 1,012,528.82** (አንድ ሚሊዮን አስራ ሁለት ሺህ አምስት መቶ ሃያ ስምንት ብር ከሰማንያ ሁለት ሳንቲም) ለውል ተቀባዩ የአገልግሎት ክፍያ የተፈጸመ ሲሆን ከዚህን ክፍያ ውስጥ በመጨረሻ ለተደረገው ቀሪ ሂሳብ ክፍያ ታክስን ጨምሮ **ብር 30,375.86** (ሠላሳ ሺህ ሶስት መቶ ሰባ አምስት ብር ከሰማንያ ስድስት ሳንቲም) የገንዘብ ምንጩ የመንግስት በጀት ነው፡፡ ይሁን እንጂ፤

- ሥራውን ለማሰራት በግዢ መጠየቂያ (Purchase Requisition) ቁጥር 5250 በቅድሚያ የተጠቀሰው የገንዘብ ምንጭ ከመንግስት በጀት ሣይሆን ከልማት አጋር ነው (BMGF)፣
- የቢሮው ፓርቲሺን ስራ ተጠናቆ ርክክቡ ነሐሴ 16 ቀን 2012 ዓ.ም ከተፈጸመ በኋላ ቢሮውን የግብርና ትራንስፎርሜሺን ኤጀንሲ (የኦሮሚያ ቅርንጫፍ ቢሮ) እየተገለገለበት ስላልሆነ ወጪው ለኤጀንሲው ዓላማ የዋለ አይደለም፡፡

### 1.2 መስፈርት

በግዢ መጠየቂያ ቁጥር 5250 ለሚሰራው ስራ የገንዘብ ምንጩ የልማት አጋሮች መሆኑ፣ ለዚህም አዲስ የቢሮ ፓርቲሺን ሥራ ለኦሮሚያ ቅርንጫፍ ቢሮ እ.አ.አ ፌብሯሪ 12/2020 እንዲሰራ ተጠይቆ በበጀት ባለቤቱ ፀድቋል፤ ሥራው በውሉና ከውሉ ጋር በተያያዙ ንድፎች መሰረት ተሰርቶ መጠናቀቁ ከተረጋገጠ በኋላ የቅርንጫ ቢሮው የኦፐሬሺን ዳይሬክተር አማኞች ባሉበት የተረከቡበት የርክክብ ቬርቫልና በተለያዩ ቀናት በሚመለከታቸው ሰራተኞች መካከል የተደረጉ የኢሜል ልውውጦች ናቸው፡፡

### 1.3 መንስኤ

ከሚመለከታቸው የባለድርሻ አካላት (ለምሳሌ የኦሮሚያ ግብርና ቢሮ/ ጋር ስራው ከመሰራቱ በፊት ተገቢው ጥናትና ምክክር በቅድሚያ አለማድረግ፤

### 1.4 የሚያስከትለው ጉዳት፣

ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፣ ወጪው ተቀባይነትን ሊያጣና ገንዘቡ ተመላሽ እንዲደረግ መንግስት ሊጠይቅ ይችላል፡፡

## 2. የስራ ውሉ በተቋረጠ ኃላፊ ስም በተመዘገበ ሲም ካርድ የተፈጸመ የአገልግሎት ሂሳብ ክፍያ ብር 3,037.04

### 2.1 ሁኔታ፤

በሞት መክንያት የስራ ውሉ በተቋረጠ የስራ ሃላፊ ስም ተመዝግበው ለነበሩት አራት ሲምካርዶች የአገልግሎት ሂሳብ ክፍያ መፈጸሙ፤

### 2.2 መስፈርት፤

የመ/ቤቱ ዋና ስራ አስፈጻሚ የኦፕሬሺንስ ሲኒየር ዳይሬክተሩን ህልፈተ ሞት አስመልክቶ ኢ.አ.አ በ31/10/2020 ያስተላለፉት የኢሜል መልዕክት እና ኢ.አ.አ ከየካቲት እስከ ሚያዚያ 2021 ክፍያ የተፈጸመባቸው የስልክ ቢሎች፡፡

### 2.2 መንስኤ፤

ወጪውን ተከታትሎ ተመላሽ አለማድረግ፣ ሲም ካርዱን በወቅቱ ተከታትሎ አለማዘጋት ወይም ለተፈቀደለት ለመ/ቤቱ ሌላ ሰራተኛ እንዲተላለፍ አለማድረግ፣ በአጠቃላይ ጠንከር ያለ ክትትልና ቁጥጥር አለመኖር፤

### 2.3 የሚያስከትለው ጉዳት፣

ተጠያቂነትን ሊያስከትል ይችላል፤ ያላግባብ የተከፈለው ገንዘብ ለመ/ቤቱ ተመላሽ ላይደረግ ይችላል፤ ወደፊት የስራ ውላቸው ከተቋረጠ የስራ ሃላፊዎች/ሰራተኞች ስም በተመዘገቡ ሲምካርዶች ከፍተኛ የሆነ የአገልግሎት ሂሳብ ክፍያ ያላግባብ ሊፈጸም ይችላል፡ ፡

## 3. በትክክለኛው የሂሳብ መደብ ያልተመዘገበ በድምሩ ብር 327,297.32 ወጪ

### 3.1 ሁኔታ

አንዳንድ የወጪ ሂሳቦች በተገቢው የሂሳብ መደባቸው/ኮዳቸው መመዝገብ ሲገባቸው በድምሩ ብር **327,297.32** ከወጪው ዓይነት/ባህሪ ጋር በማይገናኝ የሂሳብ መደቦች/ኮዶች ተመዝግበው መገኘታቸው፤

### 3.2 መስፈርት

የፌደራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 እና ቻርት ኦፍ አካውንትስ፡፡

### 3.3 መንስኤ

የወጪ ሂሳቦች በኮምፒውተር የምዝገባ ስርዓት ውስጥ ከመመዝገባቸው በፊት የሂሳቦቹን ዓይነት/ባህሪ እና የተያያዙትን ደጋፊ ማስረጃዎች በተገቢው ሁኔታ አለመገምገም፣ ከሂሳብ አያያዝ መመሪያ እና ቻርት ኦፍ አካውንት ጋር አመሳክሮ በተገቢው የሂሳብ መደብ/ኮድ አለመመዝገብ፤

### 3.4 የሚያስከትለው ጉዳት

ተዘጋጅቶ የተላለፈው የሂሳብ መግለጫ ሪፖርት ተዓማኒነትን ሊያጣ ይችላል፣ በሪፖርቱ ላይ የሚታየው የወጪ ሂሳብ ትክክለኛውን ገጽታ አያሳይም፤ በበጀት አፈጻጸም ሪፖርት ላይ ትክክለኛውን መረጃ የሚያሳይ ስላልሆነ የተሳሳተ ውሳኔ ሊያስጥ ይችላል፤

# 4. ከ1-2 ዓመት የሆናቸው የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት ብር 345,428.58

## 4.1 ሁኔታ፣

የቅድሚያ ክፍያ ተፈጽሞ በወቅቱ ሳይወራረድ በመቅረቱ ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም በድምሩ ብር 2,308,182.80 በተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት ተመዝግበው የሚገኙ ሲሆን ከዚህን መካከል በድምሩ ብር 345,428.58 (15%) ሳይወራረዱ ከ1-2 ዓመት የሆናቸው ተሰብሳቢ ሂሳቦች መኖራቸው፤

## 4.2 መስፈርት

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ተ.ቁጥር 4 የተሰብሳቢ ሒሳብ አያያዝ መሰረት የተሰብሳቢ ሒሳብ ክምችት እንዳይፈጠር ቁጥጥር መደረግ አለበት እንቅስቃሴውም በእለቱ በሂሳብ መዝገብ ላይ መመዝገብና በሒሳብ ሌጀር ላይ መወራረስ አለበት፡፡

## 4.3 መንስኤ

በመንግስት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ቅድሚያ ክፍያዎች በወቅቱ ተወራርደው ምዝገባቸውም ወቅታዊ አለመደረጉ፤

## 4.4 የሚያስከትለው ጉዳት፣

በተሰብሳቢ ሒሳብ ላይ ተገቢው ቁጥጥርና ክትትል ካልተደረገ የመንግስት ገንዘብ ለታቀደለት ዓላማ መዋሉን ለማረጋገጥ ካለመቻሉም በላይ ገንዘብ ሳይሰበሰብ ሊባክን ይችላል፤ በወቅቱ መወራረድ ሲገባው ላይወራረድ ይችላል፤

# 5 1-2 ዓመት የሆናቸው የተከፋይ ሂሳብ ክምችት ብር 289,422.13

## 5.1 ሁኔታ

በበጀት ዓመቱ ውስጥ ለተለያዩ አካላት በወቅቱ ሳይከፈል/ሳይተላለፍ በመቅረቱ ምክንያት ሰኔ 30 ቀን 2013 ዓ.ም በድምሩ **ብር 4,547,483.06** በተከፋይ ሂሳብ ክምች ተመዝግቦ የሚገኝ ሲሆን ከዚህን መካከል በድምሩ ብር 289,422.13 (6%) ከ1-2 ዓመት የሞላቸው ተከፋይ ሂሳቦች መኖራቸው፤

## 5.2 መስፈርት

የፌዴራል መንግስት መስሪያ ቤቶች የሂሳብ አያያዝ መመሪያ ቁጥር 5/2003 ተ.ቁጥር 4 የተከፋይ ሒሳብ አያያዝ መሰረት ከተለያዩ አካላት ቀንሰው ያስቀሩትን ግብርና ሌሎች ሂሳቦች ለሚመለከተው አካል ወቅቱን ጠብቀው ማስተላለፍ ፤የተከፋይ ሒሳብ እንቅስቃሴው በየእለቱ በሂሳብ መዝገብ ላይ መመዝገብና በሒሳብ ሌጀር ላይ መወራረስ ይኖርበታል፡፡

## 5.3 መንስኤ

በመንግስት የፋይናንስ ደንብና መመሪያ መሰረት ተከፋይ ሒሳቦች በወቅቱ እንዲከፈሉ ተገቢው ክትትልና ቁጥጥር አለማድረግ፤

## 5.4 የሚያስከትለው ጉዳት

የተከፋይ ሒሳብ ሁኔታ ተጣርቶ አስፈላጊው እርምጃ በወቅቱ ካልተወሰደ ሪፖርቱ ተዓማኒነትን ሊያጣና ተጠያቂነትንም ሊያስከትል ይችላል፡፡

# 6. የበጀት አፈጻጸም

## 6.1 ሁኔታ

ለ2013 በጀት ዓመት ለኤጀንሲው ልዩ ልዩ ጉዳዮች ማስፈጸሚያ የሚውል ከጸደቀው አጠቃላይ በጀት በአማካይ 85.6% ሥራ ላይ ሲውል 14.4% ስራ ላይ ሳይውል የቀረ ሲሆን የበጀት አፈጻጸማቸው ከ50% በታች የሆኑ የወጪ መደቦች መኖራቸውም ተስተውሏል፡፡

## 6.2 መስፈርት

በኤጀንሲው የፋይናንስ አስተዳደር መመሪያ (ኦክቶበር 2016) በአንቀጽ 4.2 ላይ የተቀመጡ የበጀት ዓላማዎች፡፡

## 6.3 መንስኤ

የጸደቀን በጀት ሙሉ ለሙሉ ለታለመው ዓላማ ውጤታማ በሆነ መልኩ ስራ ላይ አለማዋል፤ በበጀት እቅድ ዝግጅትና አፈጻጸም/ትግበራ የክትትል፣የቁጥጥር፣ የግምገማና የማስተካከል ስራ አለመስራት፤

## 6.4 የሚያስከትለው ጉዳት

በኤጀንሲው ሰም በጀት ተፈቅዶ በሚፈለገው መጠን ስራ ላይ ባለመዋሉ የታሰረ ስለሆነ በጀት ለሚያስፈልጋቸው ለሌሎች ፕሮጀክቶች ወይም መደበኛ ሥራዎች ተጨማሪ በጀት መንግሥት እንዳይመድብ አሉታዊ ተጽዕኖን ሊያሳርፍ ይችላል፡፡

**ኦዲት አድራጊው፤** የመ/ቤቱ የውስጥ ኦዲት ቡድን

**ያዘጋጀው፡** የሺ... ገ/ክርስቶስ

**ፊርማ፡**

**ቀን፡** 15/02/2014

**ያጸደቀው፡** በላቸው በየነ

**ፊርማ፡**

**ቀን፡** 15/02/2014